አለው። ሰውዬው ፖሊስ ጣቢያ ሄዶ አመለከተ። ፖሊስ ልብሱን ተቀብሎ ሰጠው። ልብሱን ያሳጠረበትን ዋጋ ለልብስ ሰፊው መስጠት አለበት ወይስ የለበትም? "አዎ!" ካለህ ተሳስተሃል በለው። "መክፈል የለበትም" ካለህ አሁንም ተሳስተሃል በለው" አሉት።

ተማሪው የዚህን ውስብስብ ጥያቄ መልስ ለመስማት እየጓጓ ወደ አቡ ዩሱፍ ሄደ። "ሸኽ ሆይ! አንድ ጥያቄ አለኝ" አላቸው። አቡ ዩሱፍም "ምንድን ነው ጥያቄህ?" አሉት። እሱም "አንድ ሰው ልብሱን ለልብስ ሰፊ ሰጠ።..." በማለት ጥያቄውን እያቀረበ ሳለ ሳይጨርስ አቡ ዩሱፍ "ስራውን እስከሰራ ድረስ ሊከፍለው ይገባል" አሉ። ጠያቂው "ተሳስተዋል" አላቸው።

አቡ ዩሱፍ ተገረሙና ስለጉዳዩ ጠለቅ አድርገው አስበው "በእርግጥ ክፍያ አይገባውም" አሉ። ጠያቂው "አሁንም ተሳስተዋል" አሏቸው።

አቡ ዩሱፍ ትኩር ብለው ተመለከቱትና "በአላህ ወደዚህ የላከህ ማን ነው?" አሉት። ተማሪውም ወደ አቡ ሃኒፋ እያመለከተ "እሳቸው ናቸው የላኩኝ" አለ። አቡ ዩሱፍ ወደ አቡ ሃኒፋ ሄዱና "ሸኽ ሆይ? አንድ ጥያቄ አለኝ" አሏቸው። አቡሃኒፋ ዝም አሉ።

አቡ ዩሱፍ ተነስተው ከአቡ ሃኒፋ ፊት ለፊት በጉልበታቸ ው ተንበርክከው ተቀመጡና አክብሮት በተሞላበት ሁኔታ "ሸኽ ሆይ አንድ ጥያቄ አለኝ" አሏቸው።

"ምንድን ነው ጥያቄህ?" አሉ።

"ጥያቄዬ ምን እንደሆነ ያውቁታል" አሏቸው። "የልብሱና የልብስ ሰፊው ጥያቄ?" አሉ አቡ ሃኒፋ። "አዎ" አሉ።

"ጥያቄውን ራስህ መልሰው። ሸህ አይደለህም እንዴ?" አሉ። "ሸኽ እርስዎ ነዎት" አሉ።

አቡሃኒፋም ጥያቄን መመለስ ጀመሩ። "በመጀመሪያ ልብሱን ምን ያህል እንዳሳጠረው እናያለን። ልብሱ በባለቤቱ ቁመት ልክ ያጠረ ከሆነ ስራውን በትክክል ሰርቷል ማለት ነው። ከዚያም ይህን ልብስ አላየሁም ልበለው ሲል አሰበ። ልብሱን ያሳጠረው ግን ለባለቤቱ ብሎ ስለሆነ ክፍያ ይገባዋል። ሆኖም ልብሱን ያሳጠረው በራሱ ልክ ከሆነ ወይም ልብሱን ያሳጠረው ለራሱ ብሎ ከሆነ ክፍያ አይገባውም።" አቡ ዩሱፍ የአቡ ሃኒፋን ግንባር ሳሙ። እሳቸው እስኪሞቱ ድረስም ተማሪያቸው ሆነው ቆዩ። ከዚያም የአቡ ሃኒፋን ቦታ ተክተው ህዝቡን ማስተማር ጀመሩ። ማስተዋል እንዴት ያምራል? ነገሮችን በእርጋታ መፍታት ምንኛ ድንቅ ነገር ነው?

የትዳር ጓደኛሞች፣ ወላጆች፣ ማኛጀሮችና አስተማሪዎች በአቀራረባቸው

አስተዋይ ከሆኑ ብዙ ችግሮችንና አለመግባባቶችን ይፈታሉ። መኪና ስናሽከረክር፣ ትምህርት ስናስተምር፣ ስንሸጥም ሆነ ስንገዛ ሁሌም አስተዋይ መሆን አለብን። አንዳንዴ ግን ጠንከር ማለትን የሚፈልጉ ሁኔታዎች አሉ። ምክር በምንሰጥበት ወቅትም ቢሆን። ...

ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ከተቆጡ የሚቆጡት በኃይማኖታዊ ጉዳይ ላይ ነው። ለራሳቸው ግላዊ ጉዳይ ተቆጥተው አያውቁም። የአላህ ትዕዛዝ ሲጣስ ሲያዩ ብቻ ነው የሚቆጡት። አንዴ አላህ ስራቸውን ይውደድላቸውና ኡመር ኢብኑል ኸጣብ ከአንድ አይሁድ ጋር ተገናኙ። አይሁዱ አንድ ከኦሪት /ተውራት/ የተወሰደ ፅሑፍ አነበበላቸው። እሳቸውም ደስ አላቸውና ጽፈው ለራሳቸው ያዙት። ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ዘንድ በመምጣትም ያንን ጽሑፍ አነበቡላቸው። ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ኡመር ፅሑፉ እንደማረካቸውና ከቀደምት ኃይማኖቶች አንዳንድ መመሪያዎችን መውሰድ ይቻላል ብለው ማሰባቸውን ተረዱ። ከዚያም መጽሐፍቶቻቸውን ከቁርዓን ጋር በማቀላቀል ህዝቡን ግራ ማጋባት። ኡመር ነብዩን (ሰ.ዐ.ወ) ሳይጠይቁ እንዴት ይህን ጽሑፍ በእጃቸው ፅፈው ሊያመጡ ቻሉ? ነብዩ ተቆጡ። እናም ለኡመር "ግራ ገብቶሃል እንዴ? የኸጧብ ልጅ ሆይ!" አሏቸው። የኔን ሸሪዓ ተጠራጥረኸዋል? ማለታቸው ነው። አከለውም "ነፍሴ በእጁ በሆነው ጌታ እምላለሁ። እኔ ወደናንተ የመጣሁት ተጨባጭና ግልጽ በሆነ ነገር ነው። እነሱን ምንም ነገር አትጠይቋቸው። ትክክለኛ ነገር ሲነግሯችሁ ላትቀበሉትና የተሳሳተ ነገር ሲነግሯችሁ ልትቀበሉት ትችላላችሁና። ነፍሴ በእጁ በሆነው ጌታ እምላለሁ መሳ በህይወት ቢኖር እኔን ከመከተል ውጪ ሌላ አማራጭ የለውም" አሉ። (አህመድ)

አዎ! ማስተዋል ቢኖርብንም አንዳንዴ ጨከን ማለትም ያስፈልጋል። ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) በተልዕኳቸው የመጀመሪያ ዘመን ቁረይሾች በተሰበሰቡበት ወደ ካዕባ ይመጡ ነበር። ዱዓ ያደርጋሉ። ለነሱ ምንም ዓይነት ትኩረት አይሰጧቸውም። እነሱም በተሊያዬ መንገድ ይተናኮሏቸዋል። እሳቸው ግን ሁሉንም በትዕግስት ያሳልፋሉ።

አንድ ቀን ከቁረይሾች ውስጥ የተከበረ የሚባለው ሰው ስብስቡ ውስጥ ነበርና ስማቸውን በመጥራት "ይህ ሰው ያደረሰብንን ዓይነት ችግር ማንም አድርሶብን አያውቅም። አመለካከታችንን ውድቅ አደረገ። አያት ቅድመ አያቶቻችንን ተሳደበ። ኃይማኖታችንን አወገዘ። ደረጃችንን አወረደ። አማልክቶቻችንን ተሳደበ። እኛ በእውነትም በሱ በደል ደርሶብናል" አለ። እርስ በርሳቸው እየተወያዩ ሳለ የአላህ መልዕክተኛ ጠዋፍ ለማድረግ ወደ ካዕባ መጡ። በካዕባ ዙሪያ ጠዋፉን ሲጀምሩ ያሾፉባቸው ጀመር። ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ፊታቸው ተለዋወጠ። ሆኖም ውስጣቸው በትዕግስት የተሞላ ነበርና ሁሉንም ችለው ጠዋፉን ቀጠሉ። ለሁለተኛ ጊዜ ሲያልፉ አሁንም አሾፉባቸው። ፊታቸው ተለዋወጠ። ሆኖም ዝም ብለው ጠዋፉን ቀጠሉ።

ለሶስተኛ ጊዜ ሲዞሩ አሁንም አሾፉባቸው። አሁን ትዕግስት ለነዚህ ሰዎች እንደማይሰራ ተረዱ። አጠገባቸው ሄዱና "ልብ በሉ ቁረይሾች! ነፍሴ በእጁ በሆነው ጌታ እምላለሁ። እኔ ወደናንተ የመጣሁት ይህንን ማረጃ ይዤ ነው" አሏቸው። ጀግናው መልዕከተኛና መሪ እነዚህን ቃላት ከተናገሩ በኋላ ከፊት ለፊታቸው ቆሙ።

ይህንን ዛቻ ከሐቀኛውና ከታማኙ ሰው ሲሰሙ በጣም ደነገጡና በተቀመጡበት ደርቀው ቀሩ።

ጭንቅላቱ ላይ ወፍ እንደተቀመጠበት ሰው። ሆኖም ከነሱ መካከል ለነብዩ (ሲ.ዐ.ወ) ይበልጥ መጥፎ የሆኑት ሰዎች አስተዋይ ሆኑ። "ሂድ አበል ቃሲም ሆይ! አንተ የተከበርክ ሰው ነህ። ሞኝ ሆነህ ኢታውቅም" አሏቸው። ነብዩም ሄዱ። አዎ አንድ ሰው "ተረጋጋ አስተውል..." ካለህ "ማስተዋል የራሱ ቦታ አለው" በለው። ያለ ቦታው መረጋጋት እንደሞኝ ያስቆጥራል። ምንም እንኳ የነብዩን (ሲ.ዐ.ወ) ህይወት በጥልቀት ያጠና ሰው በአብዛኛው ታጋሽ ሆነው ቢያገኛቸውም። ነገር ግን ተጠንቀቅ። ደካማና ፈሪ ሁን እያልንህ አይደለም። ለአስተዋይነት ብቻ ነው የምንጠራህ። ሌላው የማስተዋል ጥሩ ምሳሌ የሚሆነን ከቢድር ጦርነት በኋላ ባለው ወር የተከሰተው ነገር ነው።

የነብዩ (ሲ.ዐ.ወ) ልጅ የሆኑት የዘይነብ ባል አቡል አስ ዘይነብን ወደ አባቷ ወደ መዲና ሊልካት ፈለገ። የአላህ መልዕከተኛ ዘይድ ቢን ሀሪዛንና አንድን አንሷር ወደ መካ በመላክ ያአጃህ የሚባል ቦታ ላይ ጠብቀው ይዘዋት እንዲመጡ አዘዟቸው። ዘይነብ እቃዋን መሰብሰብ ጀመረች። በዚህ መሃል የአቡ ሱፍያን ሚስት ሂንድ ቢንት ኡትባ መጣች። "የሙሐመድ ልጅ ሆይ! አባትሽ ዘንድ ለመሄድ ማቀድሽን ለምን አልነገርሽኝም?" አለቻት። ሂንድ ተንኮል ታስብብኛለች ብላ በመፍራትም "እረ እኔ ወደዚያ ለመሄድ አላቀድኩም" አለቻት ዘይነብ።

"ውድ የአጎቴ ልጅ ሆይ! ወደዚያ መሄድ ካሰብሽና ለጉዞ የሚሆን ነገር ወይም ገንዘብ ካስፈለገሽ ለመጠየቅ እንዳታፍሪ። ምክንያቱም የኔና ያንቺ ግንኙነት እንደ ወንዶቹ አይደለም" አለቻት። ዘይነብ ኋላ ላይ ስትናገር "ወላሂ ይህን ያደረገችው ለተንኮል ነው ብዬ ነው ያሰብኩት። በመሆኑም እቅዴንና ወደዚያ ልሄድ ማሰቤን ደበቅኳት" ብላለች። ዘይነብ ዕቃዋን አስተካከለች። ባሏ ብቻዋን ስትሄድ ቁረይሾች ተከትለው ችግር ቢያደርሱባትስ ብሎ ፈራ። እናም ወንድሙ ኪናናህ እንዲከተላት አዘዘ። ከኪናናህ ቢን ረቢዓ ጋር በጠራራ ፀሐይ ጉዞ ጀመሩ። ይህን የተመለከቱ ሰዎች እርስ በርስ "ሙሐመድ በድር ላይ ያንን ሁሉ በደል አድርሶብን እንዴት ልጁ ወደሱ እንድትሄድ እንፈቅዳለን?" ይሉ ጀመር። በመሆኑም ተከተሏትና ዱጡዋ የሚባል ቦታ ላይ ደረሱባት። መጀመሪያ ያገኛት ሂባር ቢን አል አስወድ የሚባል ሰው ነው። በግመል ላይ እንዳለች በያዘው ጦር አስፈራራት። በዚህም እርጉዝ ነበረችና አስወረዳት ይባላል። ቁረይሾቹ መሳሪያዎቻቸውን ይዘው ወደሷ ይሮጡ

ጀመር። እሷ ግን ከባሏ ወንድም ኪናናህ በስተቀር አጠገቧ ማንም የለም። ይህን የተመለከተው ኪናናህ ቁጭ አለና ቀስቱን ለማስወንጨፍ ተዘጋጀ። "በአላህ እምላለሁ አንድ ሰው ወደኔ ቢጠጋ እገድለዋለሁ" አለ። ጥሩ ቀስተኛ ነበር። በዙሪያው ያሉ ሰዎች በማመንታት ወደ ኋላ አፈገፈጉና ከሩቅ ይመለከቱት ጀመር። እሱም አልተንቀሳቀሰም። እነሱም ሊቀርቡት አልፈለጉም።

በዚህ መሐል አቡ ሱፍያን ዜናውን በመስማቱ ከቁረይሽ የተከበሩ ከሚባሉት ጥቂት ሰዎች ጋር ደረሰ። ኪናናህ ለተኩስ መዘጋጀቱንና ቁረይሾችም ሊፋለሙት መዘጋጀታቸውን ሲያይ "አንተ ሰውዬ ቀስትህን አዙርና በጉዳዩ ላይ እንወያይ" አለው። ኪናናህም ቀስቱን አስቀመጠ። አቡ ሱፍያን ተጠጋውና እንዲህ አለው፡- "የሰራኸው ነገር ትክክል አይደለም። ይዘሃት የወጣኸው በጠራራ ፀሐይ ነው። በሙሐመድ ምክንያት በድር ላይ የደረሰብንን መከራና ስቃይ ታውቃለህ። ታላላቅ የምንላቸው ሰዎቻችን ተገድለዋል። ሴቶቻችን ያለ ባል ቀርተዋል። የሙሐመድን ልጅ በጠራራ ፀሐይ ይዘህ መውጣትህን ጎሳዎቻችን ከሰሙ እንደተጨማሪ ውርደት ይቆጥሩታል። ይሄ ሁሉ የሚደርስብን በራሳችን ስንፍናና ድክመት ነው ብለው ያስባሉ። ከአባቷ እንዳትገናኝ የማድረግ ፍላጎት እንደሌለን እምላለሁ። እሷን የመበቀል ፍላጎት የለንም። ስለዚህ ወሬው እስኪበርድና ቁረይሾች ወደ መካ እስመለስናት ብለው እስኪያስቡ ድረስ ይዘሃት ተመለስ። ከዚያ በኋላ በሚስጥር ወደ አባቷ መውሰድ ትችላለህ" አለው።

ኪናናህ የአቡ ሱፍያን ንግግር ስላሳመነው ወደ መካ ተመለሰ። ዘይነብ ወሬው እስኪበርድ ድረስ መካ ውስጥ ለጥቂት ቀናት ቆዩች። አንድ ቀን ማታ ላይ ይዟት ወጣና መንገድ ላይ ዘይድ ቢን ሀሪዛንና ባልደረባውን አገኛቸው። ሁለቱ ተቀብለው የአላህ መልዕክተኛ ዘንድ አደረሷት። አቡ ሱፍያን ምንኛ አስተዋይ ሰው ነው። የኪናናህን ቁጣ በማብረድና እሱንም ከመገደል ምናልባትም የነብዩን (ሰ.ዐ.ወ) ልጅ ሳይቀር ከመገደል ለማዳን እንዴት እንደተሳካለት ተመልከቱ። ይህ አቡ ሱፍያን ነበር። በዚያ ወቅት ካፊር የነበረው። ታዲያ እኛ ሙስሊሞችስ?

ወህይ...

ማስተዋል ሁሉንም ነገር ያስውባል። ችኩልነት ያበላሸዋል።



በሞቱትና ባሉት መካከል

በሰዎች ላይ ሽከም የሆነ አንድ ሰው ነበር። ለልጆቹ ሽከም፣ ለወንድሞቹ ሽከም፣ ለጓደኞቹ ሽከም፣ ለጎረቤቶቹ ሽከም። ደስታን አያውቃትም። ያዩት ሰዎች ሁሉ "ውድ ወንድሜ ምን ሆነህ ነው ሁሌም ቀዝቃዛ ነህ። ምንም ደስታ አይታይብህም" ይሉታል። ሆኖም ቀና መልስ አይሰጥም። አንድ ቀን ልጁ "እጅግ በጣም ጥሩ" የሚል አስተያየት መምህሩ ስለፃፈለት በጣም ተደስቶ ደብተሩን አምጥቶ አሳዬው። ሆኖም እሱ ግዴለሽ በመሆን "እና ምን ይጠበስ? ዶክትሬት ዲግሪ ያገኘህ መሰለህ እንዴ?" አለው። ልጅ የጠበቀው ምላሽ ይህ አልነበረም። አስተማሪ ነበር። አንድ አስቂኝ ተማሪ ነበረው። አንድ ቀን ይህ ተማሪ ትምህርቱም የአስተማሪውም ሁኔታ ሰልችት ይለዋል። ቀልድ አውርቶ ድብርቱን መግፈፍ ፈለገና አንድ ቀልድ አወራቸው። አስተማሪው ግን ፈገግ አላለም። በሹፈት ዓይነት ንግግር ለተማሪው "ደስ አለህ?" አለው።

አንድ ሱቅ ሲገባ የሱቁ ባለቤት "አልሀምዱሊላህ ቤተሰቦቼ ደብዳቤ ላኩልኝ!" አለው። መልስ አልሰጠውም። ይህ ሰውዬ ይሆንን ነገር ለምን ሊነግረኝ ፈለገ ብሎ እንኳ ራሱን አልጠየቀም። ወላሂ ይህ ባለ ሱቅ ይሆንን ነገር የነገረው ደስታውን ሊያካፍለው ሰለፈለገ ብቻ ነው። አንድ ጓደኛው ቤቱ ውስጥ ጋበዘውና የወለደውን ልጅ የሚያምር ልብስ አልብሶ በማምጣት "እዬው እስቲ እንዴት ነው?" አለው። ትንሽ አየት ለማድረግ ሞከረና ቅዝቅዝ ባለ ድምፅ "ማሻ አላህ አላህ የተባረከ ያድርግልህ" አለና መሬት ላይ ያስቀመጠውን ቡና አንስቶ መጠጣት ጀመረ። በእርግጥም አባትዬው የፈለገው እንዲያቅፍለት፣ እንዲስምለትና ቆንጆ ልጅ ወልደሃል እንዲለው ነበር።

ከሰዎች ጋር ባለህ ግንኙነት ነገሮችን ማዬት ያለብህ እነሱ ያን ነገር በሚመለከቱበት መንገድ እንጂ አንተ በምትመለከትበት መንገድ መሆን የለበትም። ስለዚህ ጥሩ ለሰራ ልጅህ እጅግ በጣም ጥሩ የሚለው ቃል ለሱ ከፒኤችዲ በላይ ነው። ለጓደኛህ አዲስ የወለደው ልጁ ለሱ ከመላው ዓለም በላይ ነው። ህፃኑን ባዬው ቁጥር አካሉን ከፍሎ ውስጡ ሊያስገባው ቢችል በጣም ደስ ይለዋል። ለጓደኛህ ያለህ ፍቅር ደስታውን እንድትካፈል ሊያደርግህ ይገባል። በትንሹም ቢሆን። አንዳንዴ ሰዎች በአንዳንድ ጉዳዮች ላይ ሲፈነድቁ ይስተዋላል። አንተም

በነዚህ ጉዳዮች ላይ ፍንደቃውን መካፈል አለብህ። ቀዝቃዛና ደረቅ አትሁን። ለስሜታቸው ምላሽ ስጥ። አስተያየቶችን አቅርብ። ደስታህን፣ ሀዘንህን ወይም አድናቆትህን ግለጽ። እንደ ሬሳ አትሁን። ለሰዎች ስሜት ግድ የማይለው ሰው "ልጆቼ ለምንድን ነው አጠገቤ የማይቀመጡት?" ሲል ይደመጣል። ምክንያቱም ልጆቹ ተረት ሲያወሩት መልስ አይሰጣቸውም። ትምህርት ቤት የገጠማቸውን ነገር ሲነግሩት ለግድግዳ የሚነግሩ ያህል ነው የሚሰማቸው። በመሆኑም ከሱ ጋር የመቀመጥም ሆነ የማውራት ፍላጎት አይኖራቸውም።

አንድ ሰው ከዚህ በፊት የምታውቀውን ታሪክ ቢነግርህ እንኳ ጥሩ ምላሽ መስጠት አለብህ። አብዱላህ ቢን መባረክ "ወላሂ አንድ ሰው አንድን ታሪክ ሲነግረኝ ታሪኩን እሱ ከመወለዱ በፊት የሰማሁት ቢሆን እንኳ እንደ አዲስ ነው የማዳምጠው" ብለዋል። ምን ዓይነት ድንቅ ጥበብ ነው! ከኸንደቅ ጦርነት በፊት ሙስሊሞች ምሽጎችን በመቆፈር ላይ ነበሩ። ከነሱ መካከል ጁዓይል የሚባል ሰው ነበር። ሆኖም ኑብዩ (ሲ.ዐ.ወ) ስሙን ወደ አምር ቀየሩት። ሶሃቦች በስራ ተጠምደው ሳለ እንዲህ እያሉ ይዘምራሉ።

ከጁዓይል ወደ አምር ተቀይሮ ስሙ
እገዛ የሚሰጥ ለደካማው ሁሉ።

"አምር" ሲሉ ኑብዩም አብረዋቸው "አምር" ይላሉ። "እገዛ" ሲሉ አብረዋቸው "እገዛ" ይላሉ። ሶሃቦችም ኑብዩ (ሲ.ዐ.ወ) አብረዋቸው በመሆናቸው በጣም ተደሰቱ። መሸና አየሩ በጣም እየቀዘቀዘ መጣ። ቁፋሯቸውን ቀጥለዋል። መዝሙሩንም እንደዛው።

ቃል ገብተንሊታል እኛ ለሙሐመድ በህይወት እስካለን ልንቆይ በጅሐድ!

ኑብዩም፡- "አላህ ሆይ! ህይወት የመጪው ዓለም ህይወት ነው። አንሷሮችንና ሙሃጂሮችን ማራቸው" ይላሉ። ኑብዩ (ሲ.ዐ.ወ) ቀኑን ሙሉ የነሱን ስሜት ሲጋሩ ነው የዋሉት። ሙሉ በሙሉ በአቧራ ተሸፍነው እንዲህ እያሉ ሲዘምሩ ሰሚቸው።

"አላህ ባይሻልን ጌታችን ባይፈቅድ
መች እንይዝ ነበረ የሐቁን መንገድ
ሰደቃም አንሰጥ ሶላትም አንሰግድ
በጦሩ አውድማ ላይ በውጊያው ምድር
ፅናትን ለግሰን እንዳንበገር
የቁረይሽ ፈተና ብዙ ቢሆንም
እኛም ለእምነታችን አንታገስም።"

ነብዩም አብረዋቸው "አንታገስም... አንታገስም" በማለት ስሜታቸውን ይጋሩ ነበር። ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ማንም ሰው ቀልድ ሲነግራቸው በፈገግታ ወይም በሳቅ ምላሽ ይሰጡ ነበር። አንዴ ኡመር ኢብኑል ኸጧብ ሚስቶቻቸው ብዙ ወጪ በመጠየቅ አበሳጭዋቸው። ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ዘንድ መጡና እንዲህ አሉ፡- "የአላህ መልዕከተኛ ሆይ! ድሮ የቁረይሽ ሰዎች ሳለን ሴቶቻችን በቁጥጥራችን ስር ነበሩ። አንዳቸው ተጨማሪ ወጪ ሲጠይቁን ዘለን አንገታቸውን እናንቃቸዋለን። መዲና ስንመጣ ግን ሴቶች ናቸው ወንዶችን በቁጥጥራቸው ስር የሚያውሉት። የኛ ሴቶችም ይህንን ተንኮል ከመዲና ሴቶች ተማሩ።..." ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) መሳቅ ጀመሩ። ኡመር ያወራሉ ነብዩ ይስቃሉ።

ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) የኋላ ጥርሶቻቸው እስኪታዩ ድረስ ይስቁ እንደነበር ኪሐዲሶች አንበበናል። ምንኛ ያማረ ባህሪ ነበር። አላህ በቁርዓኑ በእርግጥም "አንተ በታላቅ ፀባይ ላይ ነህ!" ብሏቸዋል። ለእኛም "በእርግጥም በአላህ መልዕከተኛ ድንቅ ምሳሌ አላችሁ" ብሎናል። ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ከሁሉም ዓይነት ሰዎች ጋር ይግባቡ ነበር። አንዳንዶቹ ከሌላ ሰው ጋር በመልካም ሁኔታ መግባባት የማይችሉ ናቸው። አንዳንዶቹ ለስሜታቸው ምላሽ አይሰጡም። ይልቁንም ቁጥብና ችኩል ይሆኑባቸዋል። ይህም ሆኖ እሳቸው ይታገሷቸዋል።

አንዴ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) በመካና መዲና መካከል በሚገኝ አል ጂራናህ በሚባል ቦታ ላይ አረፍ ብለው ነበር። ቢላል የጉዞ ኢጋራቸው ነው። አንድ ቤድዊን ቃል የገቡለትን ጉዳይ ሊጠይቃቸው መጣ። ችኩሎ ነበርና "መሐመድ ሆይ! ቃል የገባኸውን ነገር አትፈፅምም እንዴ?" አላቸው። ነብዩም (ሰ.ዐ.ወ) በትህትና "አብሽር" አሉት። አብሽር! ምን ዓይነት ማራኪ ቃል ነው። ከዚህ የበለጠ ምን ጥሩ ቃል አለ?

ሆኖም ቤድዊኑ ጥሩ መልስ አልሰጠም። ይልቁንም "ካንተ በቂ የሆነ አብሽርን ሰምቻለሁ" አላቸው። ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) በመልሱ ተናደዋል። ሆኖም ቁጣቸውን ተቆጣጠሩ። አጠገባቸው ለተቀመጡት አቡ ሙሳና ቢላል "እሱ አልፈለገም እናንተ አብሽሩ" አሏቸው።

"እሺ የአላህ መልዕከተኛ" አሉ።

አንድ ጆግ ውሃ እንዲሰጧቸው ጠየቁና እጃቸውንና ፊታቸውን ታጥበው አፋቸውን ተጉመጠመጡ። ከዚያም "ይህን ውሃ ጠጡ። ፊታችሁንና እንገታችሁን ታጠቡ እና ተደሰቱ" አሏቸው። የዚህን ውሃ በረካ በማግኘት ተደሰቱ ማለታቸው ነው። ውሃውን ወሰዱና በደስታ የተባሉትን አደረጉ። ኡሙ ሰላማ አጠገባቸው ነበረችና ከበረካው ለመቋደስ በመፈለግ "ለእናታችሁ ትንሽ አስቀሩላት" አለቻቸው። እነሱም አስተረፉና ሰጧት። ተቀብላ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዳሉት አደረገች። (ቡኻሪና ሙስሊም)

ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) በተፈጥሯቸው ደግ በመሆናቸው ከሳቸው ጋር መሆን ያስደስታል። ሁሌም ይመቻሉ። ትንሿን ድቡልቡል አፈር የተራራ ያህል አያገዝፋም። አሚሻ ለነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) አንዳንድ ወሬዎችን ታወራላቸው ነበር። እሳቸውም በትኩረት ያዳምጧታል። ብዙ ትርፍ ጊዜ የሌላቸው ቢሆንም በረሻሙና በዝርዝር ነበር የምታወራላቸው። እሳቸው ግን አስፈላጊ በሆነበት ሁኔታ አስተያየት እየሰጡ አሊሻ ወሬዋን እስከትጨርስ በትኩረት ያዳምጧት ነበር። አንዴ አንድን ታሪክ ትተርከላቸው ጀመር። ከጃሂሊያ በፊት ስለነበሩና ስለ ባሎቻቸው ባህሪ ምንም ሳይደብቁ ለመነጋገር ስለተስማሙ አስራ አንድ ሴቶች ታሪክ። በባሎቻቸው ላይ ያዩትን ሁሉ ለማውራት ተስማምተዋል። ምን አሉ?

የመጀመሪያዋ ሴት "የኔ ባል ልክ በረጂም ተራራ ጫፍ ላይ እንዳለ የማትረባ ግመል ሲጋ ነው። ከተራራው ጫፍ መድረስ በጣም አስቸጋሪ ነው። ቢደረስ እንኳ ሲጋውም ጥሩ አይደለም" በማለት ባሏን በአስቸጋሪ ተራራ ጫፍ ላይ ባለ ማንም የማይፈልገው መጥፎ ሲጋ መሰለችው። ባህሪው መጥፎ ነው። የሚያኮራ ነገር ባይኖረውም ትዕቢተኛ ነው። ስስታምና ድሃ ነው ማለቷ ነው። ሁለተኛዋ ደግሞ "እልለዬዋለሁ ብዬ ስለምፈራ የባሌን ባህሪ አልናገርም" አለች። ማለትም ባሏ ብዙ ችግሮች ስላሉበት ያንን ሁሉ ችግር ብታወራና ይህ ዜና ቢደርሰው ይፈታታል። ከሱ ጋር የምትኖረው ለልጆቿ ስትል ብቻ ነው።

ሶስተኛዋ ሴት "ባሌ ቁመቱ ረጂም ነው። ስለሱ ከተናገርኩ /እሱም ከሰማ/ ይፈታኛል። ዝም ካልኩ ደግሞ በእንጥልጥል ይተወኛል" አለች። ማለትም ባሏ ረዥም ነው። መልኩም አያምርም። ጥሩ ፀባይ የለውም። ስህተቷን ይቅር አይልም። ልክ ከላይዋ ላይ እንደተንጠለጠለ የሰላ ሰይፍ ነው። የምትኖረው በማያቋረጥ የፍቺ ዛቻ ነው። ቅሬታ ባቀረበች ቁጥር እፈታሻለሁ በማለት ያስፈራራታል። ባል ሚስቱን መያዝ ባለበት መንገድ አይዛትም። በመሆኑም በእንጥልጥል ላይ ነው ያለችው። ወይ አልተገባች ወይ አልተፈታች።

አራተኛዋ ሴት "የኔ ባል እንደ ጢሃማህ ምሽት መካከለኛ ሰው ነው። አይሞቅም አይበርድም። አልፈራውም አላዝንበትምም" አለች። እንደሚታወቀው የጢሃማህ ምሽት ነፋስና አቧራ የለውም። ለነዋሪዎች ምቹ ነው። ስለዚህ ይህቺ ሴት ባሏ ለሷ ጥሩ እንደሆነ፣ ሚዛናዊ ባህሪ እንዳለውና ጎድቷት እንደማያውቅ ተናገረች።

አምስተኛዋ "የኔ ባል ወደ ቤት ሲገባ አቦ ሸማኔ ሲወጣ ደግሞ እንደ አንበሳ ነው። ቤት ውስጥ ስላለው ነገር ምንም አይጠይቅም" አለች። ማለትም ወደ ቤት ሲመጣ እንደ አቦ ሸማኔ ነው። አቦ ሸማኔ ቸርና ንቁ ነው። ከቤት ወጥቶ ከሰዎች ጋር ሲቀላቀል ደግሞ እንደ አንበሳ ጀግና ነው። በጣም ታጋሽ ነው። ቤት ውስጥ ሚስቱን ይሄ አለቀ ይሄ ደቀቀ አይልም።

ሰድስተኛዋ በበኩሏ "የኔ ባል ምግብ አብዝቶ ይመገባል። ሲጠጣም ጭልጥ አድርጎ ነው። ሲተኛም ጥቅልል ብሎ፣ የኔን ሀዘን ለማስቀረት ሲል እጆቹን ወዲያና ወዲህ አያንቀሳቅስም" አለች። ማለትም ባሏ ብዙ ይመገባል። ለቤተሰቤ ብሎ የሚያስቀምጠው ነገር የለም። ሲጠጣም እንደዛው ነው። ለአከሌ ብሎ አያስተርፍም። ሲተኛም ቢሆን ብርድ ልብሱን ለብቻው ጥቅልል አድርጎና ለሚስቱ ምንም ሳያስቀር ነው። የሀዘን ስሜት ሲሰማትም በእጆቹ አቅፎ ሊያባብላትና የሀዘኗን መንስኤ ሊጠይቃት አይፈልግም።

ሰባተኛዋም እንዲሁ "ባለቤቴ መጥፎ ሰሪ፣ ዝርክርክና ሞኝ ነው። የሌለበት ዓይነት ጉድለት የለም። ሳወራው ይሰድበኛል ቀልድ ከቀለድኩት ጭንቅላቴን ወይም ሌላ ሰውነቴን በመምታት ጉዳት ያደርስብኛል።"

ስምንተኛዋ ሴትም "ባለቤቴ ሲነኩት እንደ ጥንቸል ነው። (ለስላሳ ነው) ሽታው ልክ እንደ ዘርነብ (ጥሩ ሽታ ያለው ሳር) ነው። እኔ ከሱ በላይ ሆኜ ነው የምኖረው። እሱ ደግሞ ከሰዎች በላይ ነው። (ለሷ ጥሩ ሰው ነው። ፍላጎቶቿን ያሟላላታል። ጀግና በመሆኑም ሰዎች ያከብሩታል። ጠንካራ ስብዕና አለው።)"

ዘጠነኛዋ "ባለቤቴ ረጂም እና ቸር ሰው ነው። ሲይፉን የሚይዝበት ትልቅ አቅማዳ ይይዛል።" (ቤቱ ሰፊ ሲሆን ሁሌም ለእንግዶች ክፍት ነው) አመዱ ብዙ ነው። (ለእንግዶቹ ምግብ ስለሚበስል ሁሌም ከቤት እሳት አይጠፋም።) ቤቱ ከስብሰባ ቦታው አጠገብ ነው። (ከቤተሰቦቹ ላለመራቅ ሲል ከጓደኞቹ ጋር የሚሰበሰበው ቤቱ አጠገብ ነው። ከሰዎች ጋር እስኪጠግብ አይበላም። (እንግዶቹን ሲያስተናግድ ብዙ አይበላም።) ሌሊቱን ስለሚፊራ አይተኛም። (ቤቱን ከጠላት ወይም ከሌላ ነገር ለመጠበቅ ሌሊቱን ቁጭ ብሎ ነው የሚያድረው።)

አስረኛዋ በበኩሏ "ባለቤቴ መሊክ ነው። መሊክ ምንድን ነው? መሊክ ከምለው ነገር ሁሉ በላይ ትልቅ ነው። ግመሎቹ በሙሉ ቤት ውስጥ ነው የሚውሉት። ጥቂቶቹ ናቸው ለግጦሽ የሚወጡት። ግመሎቹ የቢላዋ ድምጽ ሲሰሙ አበቃልን ብለው ያስባሉ።" ባለቤቷ ስሙ መሊክ ነው። የቱንም ያህል አሳምራ ብትገልፀው እሱን ፍትታዊ ሊያደርገው አይችልም። ግመሎቹ አጠገቡ ነው የሚውሉት። አልፎ አልፎ ነው ለግጦሽ የሚወጡት። በዚህም የተነሳ ለእንግዶች ለመታለብና ለመታረድ ሁሌም ዝግጁ ናቸው። ግመሎቹ የቢላዋ ድምጽ ሲሰሙ ለእንግዶች ማስተናገጃ ልንታረድ ነው ብለው ይጨነቃሉ።

አስራ አንደኛዋና የመጨረሻዋ ሴትም "ባለቤቴ አቡ ዘር ነው። ስለ አቡ ዘር ምን ማለት እችላለሁ? በርካታ ጌጣጌጦችን ስለሰጠኝ ጆሮዎቼ ሸክም በዝቶባቸዋል። እጆቼ ወፍረዋል። ዘወትር ያስደስተኛል። ከደስታዬም ብዛት በራሴ እኮራለሁ። ከበግ በስተቀር ምንም ከሌለው ድሃና ችግረኛ ቤተሰብ ነው ያገኘኝ። ሆኖም ፈረሶች፣